በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 6.5-01/11/10
Ref. No.
ቀን 013 ጥቅምት 2010
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

**ጉዳዩ፡ - <u>መመሪያ ቁጥር 128/2009 ለማስፈጸም የተዘጋጀ ጋይድላይንን ስለመላክ፤</u>**

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በግብር ከፋዮች የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎችን በአጭር ጊዜ ምላሽ ለመስጠትና ያለንን ውስን የሰው ኃብት ስጋትን መሰረት ባደረገ የታክስ ኦዲት ክዋኔ ላይ ለማሰማራት ይቻል ዘንድ በታክስ ክሊራንስ ጥያቄ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸውን ግብር ከፋዮች ለመወሰን የሚረዳ መመሪያ ነሐሴ 25 ቀን 2009 ዓ.ም. ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተላለፉ ይታወሳል።

በመሆኑም መመሪያውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ሊፈጠሩ የሚችሉ የግንዛቤ ክፍተቶችን ለመቅረፍና በአግባቡ ተግባር ላይ ለማዋል እንዲሁም በተዋረድ የሚሰጠውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለማካሄድ ያገለግል ዘንድ 22 ገጽ ጋይድላይን በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

ደስታ በቀበሰ
ም/ዋና ዳይሬክተር
አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም
ልማት ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

❖ ለዋና ዳይሬክተር
እንዲያውቁት

<u>ግልባጭ፤</u>
- ለአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዘርፍ
- ለታክስ ኦዲት አሠ/ፐሮ/ል/ድ ዳይሬክቶሬት
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለፌደራል የአገር ውስጥ ታክስ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>



ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምሥራቅ አ/አ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አ/አ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*አዳማ*</u>

- ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት

<u>*ባህርዳር*</u>

- ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*መቀሌ*</u>

- ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*ድሬዳዋ*</u>

- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*ኮምቦልቻ*</u>

- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*ጅማ*</u>

- ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

<u>*ሐዋሳ*</u>

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

## ከታክስ ክሊራንስ ጋር በተገናኘ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸውን አገልግሎቶች ለመወሰን የተዘጋጀውን መመሪያ ለማስፈፀም የተዘጋጀ ጋይድላይን

መስከረም 2010

አዲስ አበባ

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ደረጃውን የጠበቀ የተሳለጠ አገልግሎት ለመስጠት እና ገቢን ለማሳደግ የለውጥ ሥራዎችን በማከናወን በርካታ ውጤቶችን እያስመዘገበ ቢገኝም የታለመውን ያህል ውጤታማ መሆን አልተቻለም፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ የሚጠቀሰው በ2008 በጀት ዓመት ሊደረስበት ከታቀደው 17% ጠቅላላ የአገር ውስጥ ገቢ ከአጠቃላይ የተሰበሰበ የታክስ ገቢ ጥመርታ አንጻር አፈጻጸሙ 12.5% መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ አስተዳደር ስርዓቱን ማሻሻል የሚያስችል ሁሉን አቀፍ የታክስ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ነድፎ እየተገበረ ይገኛል፡፡

የታክስ ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የባለስልጣኑ የታክስ ኦዲት አሰራርን ውጤታማ ማድረግ ሲሆን በዚህም ከፍተኛ ስጋት ላይ የወደቁ ግብር ከፋዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የኦዲት ስራዎችን በማከናወንና የሕግ ተገገርነት ደረጃን በማሻሻል የታክስ ገቢን ማሳደግ ነው፡፡ አሁን ባለው የተቋሙ ተጨባጭ ሁኔታ ከ50% በላይ የሚሆነው የታክስ ኦዲት አፈጻጸም በግብር ከፋዮች የአገልግሎት ጥያቄ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ የኦዲት ሥራችን የተቋሙን የኦዲት ፖሊሲ ተከትሎ ስጋትን መሠረት በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጥ መሣለጥንና የቁጥጥር ሥራ መርሆዎችን ሚዛን ጠብቆ ከመሄድ አንፃር ክፍተት ያለበት በመሆኑ በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እያስከተለ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም ከግብር/ታክስ ግዴታ መወጣት ጋር በተያያዘ ኦዲት በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጠላቸው አገልግሎቶችን በጥልቀት በመፈተሽ በቀጣይ እንደ ስጋት ደረጃቸው ከታክስ ኦዲት በተጨማሪ በታክስ አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል እና በደንበኞች አገልግሎት የሥራ ክፍሎች የሚስተናገዱበትን አሰራር የሚደግፍ መመሪያ ቁጥር 128/2009 ተዘጋጅቶ የወረደ ሲሆን ይህንን መመሪያ በተቋም ደረጃ ወጥ በሆነ መንገድ ለመተግበር ያስችል ዘንድ ማስፈጸሚያ ጋይድላይን /Guideline/ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ ጋይድላይን በሶስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን ክፍል አንድ አጠቃላይ ሁኔታዎችን ማለትም የጋይድላይኑ አላማ ፤አስፈላጊነት ወሰኑንና የሚጠበቁ ውጤቶች፤ እንዲሁም ክፍል ሁለት በየሥራ ክፍሎቹ የሚሠጡ አገልግሎቶችና የሚጣሩ ጉዳዮች ፤ ክፍል ሶስት አጠቃላይ የዴስክ ኦዲት አሰራር ሂደትና የመረጃ አያያዝ እንዲሁም ለጋይድላይኑ ትግበራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቅፆችን በማካተት ቀርቧል፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

## ክፍል አንድ

1. ዓላማ

የተቋሙ የታክስ ኦዲት እና የሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ መሰረት ያደረገ የኦዲት አሠራር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻልና የአሠራር ወጥነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡

2. አስፈላጊነት

የታክስ ክሊራንስ እንዲሰጣቸው የአገልግሎት ጥያቄ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸው እና የሌለባቸውን መሆኑን ለመወሰን በተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 128/2009 ላይ የተካተቱ በርካታ አሰራሮች በመኖራቸው የሚመለከታቸው አመራርና ፈፃሚዎች በመመሪያው አፈጻጸም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል ሆኖ ፦

- → በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩ የአገልግሎት ዓይነቶች በደንበኞች አገልግሎት፣በታክስ ኦዲት እና በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደቶች በምን አግባብ እንደሚስተናገዱና የሚጠበቁ ግዴታዎችን ለማሳወቅና በመመሪያ ቁጥር 128/2009 ላይ በዝርዝር ያልተቀመጡ ቴክኒካል ጉዳዮችን ለማመላከት፤
- → ቀደም ሲል በተገልጋዮች ቻርተር በአንድ ክፍል እንደሚስተናገዱ የተቀመጡ አገልግሎቶች አሁን የሥጋት ስራ አመራርን በተከተለ መልኩ በተለያዩ ክፍሎች እንዲስተናገዱ የሚያደርግ በመሆኑ፤
- → የዴስክ ኦዲት አሠራርን ለመምራት እና ሥራውን በተገቢው ቅደም ተከተል ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲከናወን ለማስቻል፤
- → በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ግልጽነትን በመፍጠር ፈጣን አገልግሎት በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ለማሳደግ እንዲቻል ይህ ጋይድላይን ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3. ወሰን

ይህ የማስፈጸሚያ ጋይድላይን መመሪያ ቁጥር 128/2009ን የሚያስፈጽሙ የሀገር ውስጥ ታክስ የሥራ ዘርፎች፣ግብር ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና የታክስ ክሊራንስ እንዲሰጣቸው የአገልግሎት ጥያቄ በሚያቀርቡ ማናቸውም ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. የሚጠበቁ ውጤቶች

በዚህ ጋይድላይን መሠረት አገልግሎት በመስጠት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ውጤች ይጠበቃሉ፡-

→ ሥጋትን መሰረት ያደረገ የኦዲት አሰራር ስርዓትና ያደገ የሕግ ተገዥነት፤

→ ያደገ የተገልጋዮች እርካታ፤

→ የተሻለ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አፈጻጸም፤

→ ግልጽነትን የተላበሰና ወጥነት ያለው አሰራር፤

## ክፍል ሁለት

## በደንበኞች አገልግሎት፣በግብር አወ/አሰ/ ክትትል እና በታክስ ኦዲት የሚስተናገዱ የአገልግሎት ጥያቄዎችን በተመለከተ

### በደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት በቀጥታ የሚሰጡ አገልግሎቶችና የሚጠበቁ ግዴታዎች

በመመሪያው መሠረት እንደ ስጋት ደረጃቸው በታክስ ኦዲት እና በዴስክ ኦዲት የማይሸፈኑ የአገልግሎት ጥያቄዎች የአሰራር ሂደቱን ተከትለው በደንበኞች አገልግሎት በኩል መስተናገዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ወደ ግብር አወሳሰን፣ የታክስ ኦዲትና ሌሎች የሥራ ክፍሎች በመመሪያው መሠረት የሚተላለፉ የአገልግሎት ጥያቄዎችን እያረጋገጠ የመቀበልና የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት። በዚሁ መሠረት፡-

1. ቋሚ የድርጅት ሃብት ለመሸጥ ለሚቀርብ ጥያቄ

ግብር ከፋዮች የድርጅታቸውን ቋሚ ሀብት በሙሉም ሆነ በከፊል ለመሸጥ/ለማስተላለፍ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ጊዜ፡-

→ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ለበጀት ዓመቱ ከተመረጡ የግብር ከፋዮች ዝርዝር ውስጥ ግብር ከፋዩ የሚገኝበትን የስጋት ደረጃ መለየት፤

→ የሃብት ሽያጭ ጥያቄው ከድርጅቱ ጠቅላላ የቋሚ ንብረት ዋጋ ያለውን ድርሻ ማስላት፤

→ ለሽያጭ የቀረበውን ሃብት ምጣኔ ለማወቅ በግብር ዘመኑ መጨረሻ ከተዘጋጀው ሂሳብ የሃብትና ዕዳ መግለጫ አጠቃላይ የቋሚ ንብረት ዋጋ ውስጥ ጥያቄው የቀረበበትን ሃብት ከተገዛበት ዋጋ ላይ የተጠራቀመ እርጅና በመቀነስ መቶኛውን ማውጣት፤(ነገር ግን መረጃው በግልፅ የማይታይ ወይም ከግብር ከፋዩ ማህደር የማይገኝ በሚሆንበት ጊዜ

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No.

ግብር ከፋዩ መረጃውን እንዲያቀርብ ሊጠየቅና ይህንንም በፅሑፍ በማረጋገጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል) ፡፡

→ የሚተላለፈው ሃብት ከ50 በመቶ በላይ ወይም በታች መሆኑን በማረጋገጥ እንደ ስጋት ደረጃቸው ወደ ሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ፣

<u>ምሳሌ፡-</u>

XYZ PLC፡- ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ለተዘጋው ሂሳብ የሃብትና ዕዳ መግለጫው ላይ የተገለፀው የቋሚ ንብረት ዋጋ (ቀሪ የመዝገብ ዋጋ) ዝርዝር የሚከተለው ነው፡፡

| የዕቃው ዓይነት | የተገዛበት ዋጋ | የተጠራቀመው እርጅና ቅናሽ | በ30/10/2008 ቀሪ የመዝገብ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| ሕንፃ | 2,000,000 | -600,000 | 1,400,000 |
| ማሽነሪ | 800,000 | -250,000 | 550,000 |
| ተሽከርካሪዎች | 1,200,000 | -585,600 | 614,400 |
| ድምር | **4,000,000** | **-1,435,600** | **2,564,400** |

ድርጅቱ ካሉት 5 ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከ3 ዓመት በፊት በብር 300,000 የተገዛውን ኮድ 03-***1/አ.አ መስከረም/2009 ለመሸጥ አገልግሎት ቢጠይቅ፡-

| የዕቃው ዓይነት | የተገዛበት ዋጋ | የተጠራቀመ እርጅና ቅናሽ | በ30/10/2008 ቀሪ የመዝገብ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| ኮድ 03-***1/አ.አ | 300,000 | (146,400) | 153,000 |
| (153,000 /2,564,400)*100= 6% | | | |

የሚሸጠው ንብረት ቀሪ የመዝገብ ዋጋ በ30/10/2008 ዓ.ም በድርጅቱ የሂሳብ መግለጫ ከተመዘገበው ጠቅላላ ቀሪ ቋሚ ንብረት ዋጋ ብር 2,564,400 አንፃር 6% በመሆኑ በመመሪያው መሠረት ወደ ግብር እወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የስራ ሂደት ይተላለፋል፡፡

- የድርጅት ሃብት ለማስተላለፍ/ለመሸጥ የበጀት ዓመቱ እንደተዘጋ ወይም በሚቀጥለው በጀት ዓመት መሀል ላይ ለሚቀርብ የአገልግሎት ጥያቄ የሚተላለፈው ሀብት ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ከአጠቃላይ የቋሚ ንብረት ዋጋ ያለውን ምጣኔ ለማስላት የምንጠቀመው መጨረሻ ለተዘጋው የግብር ዘመን የቀረበው የሃብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ ነው፡፡

2. <u>ድርጅት ሙሉ ለሙሉ/በከፊል ለመዝጋት ለሚቀርብ ጥያቄ</u>

ድርጅትን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመዝጋት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ፡-

→ ድርጅቶች ማመልከቻ እና በውጭ ኦዲተር የተዘጋጀ Liquidation statement ማቅረባቸውን ማረጋገጥ/እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

→ ለበጀት ዓመቱ በተለየው የድርጅቶች የስጋት ደረጃ መሠረት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኙትን ወደ ታክስ ኦዲት እና መካከለኛና ዝቅተኛ ላይ የሚገኙትን ወደ ግብር አወሳሰን ማስተላለፍ፣

3. <u>የተለያዩ ህጋዊ ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሃድ ለሚቀርብ ጥያቄ</u>

የተለያዩ ህጋዊ ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሃድ ጥያቄያቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ፡-

→ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ለበጀት ዓመቱ ከተመረጡ የግብር ከፋዮች ዝርዝር ውስጥ ግብር ከፋዩ የሚገኝበትን የስጋት ደረጃ መለየት፣

→ ዋናው ድርጅት የተዋሃዱን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የሚዋሃድ መሆኑን/አለመሆኑን ድርጅቶቹ ከሚያቀርቡት የውህደት ማመልከቻ ውልን በመቀበል ማረጋገጥ፣

→ ዋናው ድርጅት የተዋሃዱን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የማይዋሃድ ከሆነ የስጋት ደረጃው ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ቢሆንም የቀረበው የአገልግሎት ጥያቄ ድርጅት እንደ መዝጋት ተቆጥሮ በመመሪያው መሠረት ወደ ታክስ ኦዲት የሥራ ሂደት ማስተላለፍ፣

→ ዋናው ድርጅት የተዋሃዱን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የሚዋሃድ ሲሆን፡-

ሀ. ለከፍተኛ ግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ደረጃው ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ቢሆንም ብቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል ይስተናገዳል። ነገር ግን አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት ከግ/ከፋዩ ጋር በተገናኘ በታክስ ህግ ማስከበር ክፍል በእጅ የሚገኝ መረጃ ካለ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ አገልግሎቱ በቀጥታ የተሠጠ ስለመሆኑ መረጃው ለታክስ ኦ/ም/ሥራ አስኪያጅ በማስታወሻ መተላለፍ አለበት።

ለ. ለመካከለኛ ግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ደረጃው ከፍተኛ ከሆነ ወደ ታክስ ኦዲት ይተላለፋል።



Ethiopian Revenues and Customs Authority

ሐ. ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ደረጃው መካከለኛም ሆነ ዝቅተኛ በቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል ይስተናገዳል፡፡

4. ሌሎች በደንበኞች አገልግሎት የሚከናወኑ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ

የባለስልጣን መ/ቤቱ በታክስ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አካቶ ከሚያከናውናቸው የለውጥ ሥራዎች መካከል በከፍተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ ቤት በ Self Audit የትኩረት እርምጃ የሚሰራው ይገኝበታል፡፡ ይህም በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ተመዝግበው ዕውቅና በተሰጣቸው የውጪ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርገው የሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ አገልግሎት የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፡፡ ወደፊት በከፍተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአፈፃፀም ተሞክሮው የተሣካ ሆኖ ወደ ሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች ሊስፋፋ የሚችል ሲሆን ይህንን በተመለከተ የሚዘጋጁ ቅድመ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ተጠናቀው ወደ ትግበራ ሲገባና አሠራሩን ተከትለው የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎችን የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እንደሚቀርበው የአገልግሎት ጥያቄና የስጋት ደረጃ እየመዘነ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

በግብር አወ/አሰ/ ክትትል የስራ ሂደት ምላሽ የሚሰጣቸው አገልግሎቶችን በተመለከተ

በአፈፃፀም መመሪያው ቁጥር 128/2009 ላይ በግብር አወ/አሰ/ክት የስራ ሂደት በኩል ውሳኔ እንዲሰጣቸው የሚተላለፉ የአገልግሎት ጥያቄዎች እንደ የአገልግሎት ጥያቄዎቹ ባህሪ በክፍል ሦስት ላይ በተዘረዘሩ የአሠራር ሂደቶች መሠረት የቅድመ ዴስክ ኦዲት/አወሳሰን ትንተናዎችን በማድረግ ልናተኩርባቸው የሚገቡ የስጋት አመላካች የሂሳብ ቋቶችን መለየት የሚጠበቅ ሆኖ ወደ ዝርዝር ስራው ተገብቶ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የሚከተሉትን ቅድሚያ ሰጥቶ ማየት ይጠበቃል፡፡

1. ድርጅት ለመዝጋት/ንግድ ፈቃድ ለመመለስ ለሚቀርብ ጥያቄ

1.1 ስራ ያልጀመረ ድርጅትን በተመለከተ

ግብር ከፋዩ በተመዘገበበት የንግድ ፍቃድ ምንም ዓይነት ስራ አለመስራቱን ገልፆ ይህንን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት (ከዕዳ ነፃ ክሊራንስ) የጠየቀ እንደሆነ የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የስራ ክፍል የዴስክ ኦዲት ሥራዎችን በማከናወን ከዚህ በታች የተቀመጡት እና ሌሎች ነጥቦች በማጣራት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

→ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ብቻ አውጥተው የንግድ ስራ ፈቃድ ያላወጡ በሚሆኑበት ጊዜ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በወሰዱበት የታክስ ማዕከል አድራሻ/ወረዳ ወይም ከግ/ከፋዩ ወቅታዊ የመኖሪያ አድራሻ(ሕጋዊ አድራሻ የመቀየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ) የንግድ ስራ ፈቃድ ከሚሰጠው አካል የንግድ ፈቃድ ስለመኖሩ በቀጥታ በደብዳቤ ጠይቆ ማረጋገጥ፣

→ የንግድ ስራ ፈቃድ ያወጡ ሆነው የይዘጋልኝ ጥያቄ በሚሆንበት ጊዜ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ስለማከናወናቸው በኢንተለጀንስ የስራ ክፍል እጅ የሚገኝ መረጃ ካለ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፣

→ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው (የንግድ ስራ ፈቃድ ሲያወጡም ሆነ ሳያወጡ) የይዘጋልኝ ጥያቄ ከሆነ በኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙትን የቀረጥ ነፃ መብቶች ላይ የተሰጠ ውሳኔ ማስረጃ ሲቀርብ፣

→ የአገር ውስጥም ሆነ የውጪ ሀገር ግዥ እና ሽያጭ ስለመኖሩ በሲስተም(SIGTAS፣ ASYCUDA፣ ከተቋሙ የታክስ መረጃ ቋት/portal ወ.ዘ.ተ) እና በማንዋል ማረጋገጥ የሚጠበቅ ሆኖ መረጃውን ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታ ካጋጠመ ከታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማካሄድ፣

→ ድርጅቱ ስራ አለመጀመሩ በዴስክ ኦዲት ከተረጋገጠ አገልግሎቱ እንዲያገኝ ወደ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ማስተላለፍ፣

### 1.2 <u>ድርጅት ለመዝጋት</u>

በንግድ ሥራ ውስጥ ቆይተው ድርጅታቸውን ለመዝጋትና የዕዳ ነጻ ማስረጃ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ግ/ከፋዮችን በተመለከተ፦

→ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት መቅረቡን ወይም ድርጅቱ በበጀት ዓመቱ መሀል የሚዘጋ ከሆነ ለከፊል ዓመት የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ መኖሩን ጭምር ማረጋገጥ፣

→ ድርጅቱ ካሳወቀው ግዥ/ሽያጭ ጋር ልዩነት ስለመኖሩ በሲስተም(SIGTAS፣ ASYCUDA፣ከተቋሙ የታክስ መረጃ ቋት/portal ወ.ዘ.ተ) እና በማንዋል ማረጋገጥ የሚጠበቅ ሆኖ መረጃውን ለማግኘት አስቸጋሪ ሁኔታ ካጋጠመ ከታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማካሄድ፣

→ በዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ላይ እንደ ወጪ ተመዝግበው ከቀረቡት ዝርዝር የወጪ ርዕሶች ውስጥ በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ መሠረት መያዝ የሌለበት ወጪ መኖሩን



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን ቡ
Ethiopian Revenues and Customs Authority

የማጣራት ስራ ማከናወን፣ መያዝ የሌለበት ወጪ መኖሩ ከተረጋገጠ ሊከፈል የሚገባውን ግብር/ታክስ አስተካክሎ መጠየቅ፣

→ የዓመቱ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የተጠቀሰው የሽያጭ/የገቢ መጠንን በየወሩ ከቀረበው የቫት ማሳወቂያ(በቫት እና ያለቫት ሽያጮች ድምር) ጋር በማነፃፀር ትክክለኛ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥና ግብር/ታክስ ሊያስጠይቅ የሚችል ልዩነት መኖሩ ከተረጋገጠ በልዩነቱ መሠረት ተጨማሪ ግብር/ታክስ መጠየቅ፣

<u>ምሳሌ፡-</u>

XYZ PLC:- በ2008 በጀት ዓመት መዝጊያ ሪፖርት ሲያቀርብ የሽያጩ መጠን 9 ሚሊዮን ቢሆን እና በየወሩ ያሣወቀው የቫት እና ያለቫት ሽያጮች ድምር 10 ሚሊዮን ቢሆን ሁለቱ የሽያጭ መጠኖች እኩል አለመሆናቸውን እናረጋግጣለን፡፡ በሁለቱ መካከል በሚታየው የ1 ሚሊዮን ያላሳወቁት ሽያጭ እንዳለ ታሳቢ በማድረግ በሽያጭ ልዩነት መሠረት በዓመቱ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ አንድ ሚሊዮን በመደመርና 30% ተከፋይ የግብር መጠን በማስላት ይህንንም ውጤት ቀድሞ ከተከፈለው የዓመቱ የታክስ መጠን ላይ በመቀነስ ልዩነቱን ክፍያ እንዲፈፀምበት ማድረግ ይገባል፡፡ በንግድ ትርፍ እና በተ.እ.ታ/ተ.ኦ.ታ ሽያጭ መጠን ላይ ልዩነቶች ኖረው ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች በአግባቡ ያልተከፈሉ ከሆነ መከፈል የሚገባውን የተ.እ.ታ/ተ.ኦ.ታ ማስላት ይጠበቃል፡፡ ይህን በምናደርግበት ጊዜ በሂሳብ አያያዝ ላይ ግብር/ታክስ ሊያስጠይቁ የማይችሉ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሣቢ በማድረግ በቅድሚያ የልዩነቱን ምክንያት ግብር ከፋዩ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ማድረግና በግብር ታክስ ሕግጋት መሠረት ምክንያታዊ የሆኑ ገለፃዎች ከቀረቡ ከቅርብ ኃላፊ ጋር በመወያየት የማስተካከያ ስራ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦችን መመልከት ይገባል፡-

→ በዓመቱ ውስጥ የተከፈለው የቅድመ ግብር መጠንን (Withholding tax) በዓመቱ ከተገለፀው ሽያጭ/ገቢ ጋር በማመሳከር የሒሳብ ምርመራ ማከናወን፣

→ በሁሉም የታክስ አይነቶች ላይ የግብር ዕዳ አለመታየቱን ማረጋገጥ፣

→ ያልተሸጡ ዕቃዎች/Stock/ መኖራቸውን ከሂሳብ መግለጫ ላይ በመመልከት በገበያ ዋጋ መሠረት እንደተሸጡ ታሳቢ በማድረግ ሊከፈል የሚገባውን ግብር/ታክስ በድጋሚ አስተካክሎ ማስላት፣

- → ግብር ከፋዩ ካቀረበው የሂሳብ መግለጫ በመነሳት የዕርጅና ዘመናቸውን የጨረሱ ቋሚ ንብረቶች ካሉ ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፉ በሚችሉበት አማካይ የገበያ ዋጋ መሠረት በማስላት ሊከፈል የሚገባውን ግብር/ታክስ በድጋሚ አስተካክሎ ማስላት፣
- → የግብር ከፋዩን/ ድርጅቱን የባንክ ሂሳብ ሚዛንና በግብር ከፋዩ የሒሳብ መግለጫ የቀረበውን የሽያጭ መጠን በማነፃፀር ተጨማሪ ጥያቄዎች ማቅረብ፣
- → ያሣተመውን ደረሰኝ መመለሱን ማረጋገጥ፣
- → ካሽ ሬጅስተር ማሽን ጋር ተያይዞ ተመላሽ ማድረጉን ማረጋገጥ፣
- → የእርጅና ቅናሽ ቋሚ ንብረት የመዝገብ ዋጋ horginal ደረሰኝ ጋር ማገናዘብ፣
- → የኪራይ ወጪ ካለ ውል/ደረሰኝ ማየት፣
- → የወለድ ወጪ ካለ የብድር ውል እና ብድሩ ገቢ ለሚያመነጨው ሥራ የዋለ መሆኑን መመልከት፣
- → የደሞዝ ወጪ/Payroll expense ካለ ደጋፊ ሰነዶች/የቅጥር ደብዳቤ፣እንደ ፔሮልና የደመወዝ ገቢ ግብር የተከፈለበትን ደረሰኞች መመልከት ወ.ዘ.ተ፣

2. <u>የተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ</u>

የተመላሽ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ የጥያቄዎችን ዓይነት መሠረት በማድረግ ቀጥሎ በተጠቀሰው መልኩ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቃል፡-

2.1 <u>በላኪዎች የተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ</u>

የተመላሽ ጥያቄው በላኪነት የሥራ ዘርፍ ላይ በተሰማሩ ግ/ከፋዮች የቀረበ ከሆነ፡-

- → ዕቃው ወደ ውጭ ሀገር የተላከ መሆኑን ማረጋገጥ፤እንዲሁም ከተገዛው ዕቃ ውስጥ የትኞቹ ተላኩ የትኞቹ አገር ውስጥ ተሸጡ / ወደ ውጭ አልተላኩም የሚለውን በመረጃ በዝርዝር መለየት፣
- → የተ.እ.ታክስ የተከፈለባቸው የሃገር ውስጥ ግዥ የተፈፀመባቸው ኦርጅናል ደረሰኞች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- → የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖች፣ ኤይር ዌይ ቢል/Air way Bill/ኦርጅናል ደረሰኞች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
- → የባንክ ፈቃድ /Bank Permit/፣ የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ኦርጅናል ደረሰኞችን መመልከት፣
- → የሽያጭ ደረሰኝ ፓድ/ካሽ ሬጅስተር ደረሰኝ፣ Attachment ወ.ዘ.ተ መኖሩን ማረጋገጥ፣

→ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሲስተም መረጃ ጋር ማመሳከር፣
→ የቀረበው ደረሰኝ እውነተኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣
→ ድርጅቱ የግብር ውሳኔ የደረሰው ወይም የሚከፈል የታክስ ዕዳ ስለመኖሩ ማረጋገ፣
→ የተመላሹን ትክክለኛነት በታክስ ህጎች መሠረት አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት እና ከተመላሽ ጋር ተያይዘው የወጡ ማንኛውም መመሪዎችን አገናዝቦ መፈፀም ይጠበቃል፣

### 2.2 <u>በገቨው ተይዘው የተ.እ.ታ. ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ</u>

በገኘው ተይዞ በግ/ከፋዩ የሚቀርበውን የተመላሽ ጥያቄ በተመለከተ፡-
→ በወኪል አማካኝነት የተሰበሰበ የተ.እ.ታ መኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የተ.እ.ታክስ የተከፈለባቸው የሃገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ግገር የተፈጸመባቸው ኦርጅናል ደረሰኞችና ቫውቸሮች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣
→ የተ.እ.ታክስ ተቀናሽ የተደረገበት ደረሰኞች ኮፒ መኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የሽያጭ ደረሰኝ ፓድ መኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የቀረበው ደረሰኝ እውነተኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣
→ ተመላሽ የተጠየቀበት ወር የተ.እ.ታክስ ያሳወቀበት ቅጽ መኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሲስተም መረጃ ጋር ማመሳከር፣
→ ድርጅቱ የግብር ውሳኔ የደረሰው ወይም የሚከፈል የግብር ዕዳ ስለመኖሩ ማረጋገጥ፣
→ የተመላሹን ትክክለኛነት በታክስ ህጎች መሠረት አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት እና ከተመላሽ ጋር ተያይዘው የወጡ ማንኛውም መመሪዎችን አገናዝቦ መፈፀም ይጠበቃል፣

### 2.3 <u>በባለልዩ መብት /በጎ አድራጎት/ተጠቃሚ ድርጅቶች የተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ</u>

በባለልዩ መብት ተጠቃሚዎች የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄን በተመለከተ፡
→ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ በፍትህ ሚኒስቴር ከበጎ አድራጎት ኤጀንሲ የተፈቀደለት ባሊልዩ መብት መሆኑን ማረጋገጥ፣
→ የተ.እ.ታክስ የተከፈለባቸው የሃገር ውስጥ ግገር የተፈፀመባቸው ኮፒ ደረሰኞች ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣
→ የሚቀርቡ ደረሰኞች በሚመለከተው ኃላፊ ተረጋግጦ መቅረቡን ማረጋገጥ፣
→ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሲስተም መረጃ ጋር ማመሳከር፣
→ የቀረቡ ደረሰኞች ሕጋዊነት በሲስተም(ኦራክል) ማረጋገጥ፣



Ethiopian Revenue ... Recor...

→ ድርጅቱ የግብር ውሳኔ የደረሰው ወይም የሚከፈል የግብር ዕዳ ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤
→ የተመላሹን ትክክለኛነት በታክስ ህጎች መሠረት አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት እና ከተመላሽ ጋር ተያይዞው የወጡ ማንኛውም መመሪዎችን አገናዝቦ መፈፀም ይጠበቃል፣

## 2.4 የቅድመ ግብር ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ

የቀረበው የተመላሽ ጥያቄ ከቅድመ ግብር ጋር የተያያዘ ሲሆን፡-

→ የቀረበው ጥያቄ ከሶስት የበጀት ዓመት በላይ አለመሆኑን ማረጋገጥ፣
→ የውጪ ኦዲተር የምርመራ ሪፖርት መቅረቡን ማረጋገጥ፣
→ የቅድመ ግብር ተቀናሽ የተደረገበት ደረሰኞችና ቫውቸሮች ኮፒ መኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የቀረቡ ደረሰኞች ሕጋዊነት በሲስተም(ኦራክል) ማረጋገጥ፣
→ ድርጅቱ ውሳኔ የደረሰው ወይም የሚከፈል ዕዳ አለመኖሩን ማረጋገጥ፣
→ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሲስተም መረጃ ጋር ማመሳከር፣
→ የተመላሹን ትክክለኛነት በታክስ ህጎች መሠረት አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት እና ከተመላሽ ጋር ተያይዘው የወጡ ማንኛውም መመሪዎችን አገናዝቦ መፈፀም ይጠበቃል፣፣

## 3. ቋሚ የድርጅት ሃብት ሽያጭ /ቬር ማስተላለፍ

ቋሚ የድርጅት ሀብትን ከማስተላለፍ ጋር በተገናኘ የሚተላለፈው ሀብት ከ 50 በመቶ በላይ ወይም በታች ቢሆንም የግብር ከፋዩ የሥጋት ደረጃ ከፍተኛ እስካልሆነ ድረስ በግብር አወ/አሰ/ክት የሥራ ሂደት በኩል በዴስክ ኦዲት ተጣርቶ እንደሚስተናገድ በመመሪያው በግልጽ ተቀምጧል። ይህም ምንም እንኳን የሚተላለፈው ሀብት መጠን አነስተኛ ቢሆንም በተደጋጋሚ የሀብት ማስተላለፍ ጥያቄ የሚያቀርቡ ግ/ከፋዮችን ትኩረት ለመስጠት ጭምር ታሳቢ ያደረገ ነው። በመሆኑም በዴስክ ኦዲት አሠራራችን ሂደት እንደ ግ/ከፋዩ የሥጋት ደረጃና የሚተላለፈው ሀብት መጠን(እንደ ግ/ከፋዩ የሀብት ዝውውር ጥያቄ መጠን 10%፣20%፣30%፣40% ወ.ዘ.ተ) የዴስክ ኦዲት ወሰናችንን በማስቀመጥና የዴስክ ኦዲት ጥልቀት ደረጃውን በማስፋትና በማጥበብ ከታች የተዘረዘሩት ነጥቦች በማጥራት በታክስ ህጎች መሠረት አረጋግጦ ውሳኔ መስጠት ይጠበቃል።

→ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት መቅረቡን ማረጋገጥ፣
→ የግብር ከፋዩን የቀድሞ ግብር የመክፈል ታሪክ መረዳት፣
→ የትርፍ ድርሻ መክፈሉን ወይም ለካፒታል ማሳደጊያነት መዋሉን ማረጋገጥ ፣

→ አቤቱታ ላይ አለመሆኑ ማረጋገጥ፣

→ የካፒታል ንብረቶችን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የከተሞችና እና የክልል የመሬት አስተዳደር ስራዎችን የሚያከናውኑ የመንግስት መ/ቤቶችና እንዲሁም ሕጋዊ ፈቃድ ካላቸው የሃብት/ንብረት ገማቾች መቅረቡን ማረጋገጥ፣

ምሳሌ 1፡- <u>አክሲዮን/ሼር ማስተላለፍ</u>

XXX ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ኩባንያ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሀምሌ 1/1989 ዓ.ም በሁለት ባለአክሲዮኖች በአጠቃላይ የተከፈለ ካፒታል 1,000,000 ብር(1000 ሼር እያንዳንዱ 1000 ብር ተመን) የተቋቋመ ነው፡፡ ሀምሌ/2007 ዓ.ም በባለ አክሲዮኖቹ በተደረገ ስምምነት መሰረት ለአዲስ አባላት 400 ሼሮች እንዲተላለፉ ተወስኗል፡፡ በዚሁ መሰረት ከካፒታል ዋጋ ዕድገት ጋር በተገናኘ ታክስ ለመወሰን፡-

| | | |
|---|---|---|
| የተሰጠው/የተላለፈው ሼር የአንዱ ዋጋ | 1,850 | |
| የተላለፈ ሼር ብዛት | 400 | |
| የተላለፈ ሼር ጠቅላላ የመሸጫ ዋጋ | | 740,000.00 |
| የተላለፈ ሼር ብዛት | 400 | |
| የተላለፈው ሼር የአንዱ ዋጋ/Cost/share | 1000 | |
| የተላለፈ ሼር ጠቅላላ መነሻ ዋጋ/Cost of share | | 400,000.00 |

ሲደመር የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ/Inflation

| ዓመት | የተላለፈ ሼር ጠቅላላ መነሻ ዋጋ | የወለድ መክፈያ መጠን inflation rate | በዓመቱ የወራት ብዛት | የዋጋ ግሽበት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1990 | 400,000.00 | 3.00% | 12 | 12,000.00 |
| 1991 | 412,000.00 | 3.00% | 12 | 12,360.00 |
| 1992 | 424,360.00 | 3.00% | 12 | 12,730.80 |
| 1993 | 437,090.80 | 3.00% | 12 | 13,112.72 |
| 1994 | 450,203.52 | 3.00% | 12 | 13,506.11 |
| 1995 | 463,709.63 | 3.00% | 12 | 13,911.29 |
| 1996 | 477,620.92 | 3.00% | 12 | 14,328.63 |
| 1997 | 491,949.55 | 3.00% | 12 | 14,758.49 |
| 1998 | 506,708.03 | 3.00% | 12 | 15,201.24 |
| 1999 | 521,909.27 | 3.00% | 12 | 15,657.28 |
| 2000 | 537,566.55 | 3.00% | 4 | 16,127.00 |
| 2001 | 553,693.55 | 3.00% | 12 | 16,610.81 |
| 2002 | 570,304.35 | 3.00% | 12 | 17,109.13 |
| 2003 | 587,413.49 | 3.00% | 6 | 8,811.20 |

| ዓመት | የተላለፈ ሼር ጠቅላላ መነሻ ዋጋ | የወለድ መክፈያ መጠን inflation rate | በዓመቱ የወራት ብዛት | የዋጋ ግሽበት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 2003 | 596,224.69 | 4.00% | 6 | 11,924.49 |
| 2004 | 608,149.18 | 4.00% | 6 | 12,162.98 |
| 2004 | 620,312.17 | 5.00% | 6 | 15,507.80 |
| 2005 | 635,819.97 | 5.00% | 12 | 31,791.00 |
| 2006 | 667,610.97 | 5.38% | 3 | 8,979.37 |
| 2006 | 676,590.34 | 5.54% | 3 | 9,370.78 |
| 2006 | 685,961.11 | 5.53% | 3 | 9,483.41 |
| 2006 | 695,444.52 | 5.55% | 3 | 9,649.29 |
| 2007 | 705,093.82 | 5.59% | 7 | 22,991.93 |
| | | | | 328,085.75 |

ሲቀነስ የተላለፈ ሼር የተስተካከለ መነሻ ጠቅላላ ዋጋ 728,085.75

ታክስ የሚከፈልበት ትርፍ/ኪሳራ 11,914.25

የሚከፈል ታክስ 30% 3,574.27

በተጨማሪም እስካሁን ያልተከፋፈለ ትርፍ የተገኘ እንደሆነ እና ለካፒታል ማሳደጊያነት ስለመዋሉ የሚያረጋግጥ ሰነድ እስካልቀረበ ድረስ በገቢ ግብር አዋጅ እና በንግድ ህግ ላይ በተቀመጡ ድንጋጌዎች መሠረት የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር መወሰን ይጠበቃል፡፡

- ቀደም ሲል የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር አፈጻጸም በተመለከተ ከገ/ኢ/ል/ሚ የተላለፈውን ውሳኔ አስመልክቶ በባለስልጣኑ በቁጥር 6.1.0/849/08 በቀን ታህሳስ 19/2008 ዓ.ም በተሰጠ የአፈጻጸም ማብራሪያ ከ2005 የግብር ዘመን ጀምሮ የትርፍ ድርሻ ገቢው ለካፒታል ማሳደጊነት ስለመዋሉ የሚያስረዳ ማስረጃ በሰነዶች ምዝገባና ማ/ጽ/ቤት ጸድቆ የተመዘገበ የባለአክሲዮኖች ቃለ-ጉባኤ እና የኩባንያው/የድርጅቱ ካፒታል አድጎ የተመዘገበ ስለመሆኑ የግብር ዘመኑ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ተሟልቶ ካልቀረበ የትርፍ ድርሻው እንደተከፋፈለ ተቆጥሮ ግብሩ መደበኛውን የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓትን ተከትሎ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

በሌላ መልኩ ከሼር ማስተላለፍ ጋር በተገናኘ አንድ ድርጅት በተለያየ ጊዜ ካፒታሉን ሊያሳድግና ሼሩን የሚስተላልፉት አባላትም (ነባር እና በኋላ የገቡ አዲስ አባላት) እንደዚሁ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የካፒታል ዋጋ ዕድገት ታክስ ከመወሰናችን በፊት ድርጅቱ ካፒታሉን መቼና በምን መልኩ እንዳሳደገ እንዲሁም የእያንዳንዱ ባለአክሲዮን [illegible] መጠን እና ሼሩን የሚያስተላልፈው ማን እንደሆነ መለየት ይጠበቃል፡፡

ይህም የድርጅቱ አጠቃላይ ካፒታል (Shareholders Capital) እና የእያንዳንዱ ባለአክሲዮን ሼር መጠን የሚለውጥ በመሆኑ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ለማድረግ መነሻ የምናደርገው የሼር ዋጋ በመለየት ውሳኔ ለመስጠት ያስችላል ማለት ነው።

- ስለሆነም የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ለማስላት የምንጠቀመውም በንግድ ባንኮች በሚቀመጥ ገንዘብ ላይ የሚታሰብ የወለድ ምጣኔ/Deposit rate/ ሆኖ ይህም በየጊዜው እየተሻሻለ ከብሔራዊ ባንክ የሚተላለፈውን በተቀማጭ ገንዘብ ላይ የሚከፈለው የወለድ ምጣኔ መሠረት በማድረግ መሆኑን እንገልጻለን።

ምሳሌ 2፦ <u>ቋሚ የድርጅት ሃብት ማስተላለፍ/ ሽያጭ</u>፣

XYZ ኃ.የተ.የግ.ኩባንያ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1995 ዓ.ም በአስር ባለአክሲዮኖች የተቋቋመ ድርጅት ነው። በባለ አክሲዮኖቹ በተደረሰ ስምምነት መሰረት በድርጅቱ ሥም የሚገኘውን አንድ ሕንጻ በሽያጭ ለZZZ ትራዲንግ እንዲተላለፍ ወስኗል። በዚሁ መሰረት ከድርጅቱ የሚጠበቅ ታክስ ለመወሰን መረጃው በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፦

| | | |
|---|---|---|
| የቋሚ ንብረቱ የሽያጭ ዋጋ | | 1,400,000 |
| ቋሚ ንብረቱ በሀምሌ/1998 የተገዛበት ዋጋ | 1,000,000 | |
| ቋሚ ንብረት ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ | 450,000 | |
| የቋሚ ንብረት የመዝገብ ዋጋ | 550,000 | |

**ሲደመር የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ**

| ዓመት | የተላለፈ ሀብት ጠቅላላ መነሻ ዋጋ | የወለድ መክፈያ መጠን inflation rate | በዓመቱ የወራት ብዛት | የዋጋ ግሽበት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1999 | 1,000,000 | 3.00% | 12 | 30,000.00 |
| 2000 | 1,030,000 | 3.00% | 12 | 30,900.00 |
| 2001 | 1,060,900 | 3.00% | 12 | 31,827,00 |
| 2002 | 1,092,727 | 3.00% | 12 | 32,781.81 |
| 2003 | 1,125,509 | 3.00% | 6 | 16,882.63 |
| 2003 | 1,142,391 | 4.00% | 6 | 22,847.83 |
| 2004 | 1,165,239 | 4.00% | 6 | 23,304.79 |
| 2004 | 1,188,544 | 5.00% | 6 | 29,713.60 |
| 2005 | 1,218,258 | 5.00% | 12 | 60,912.88 |
| 2006 | 1,279,171 | 5.38% | 3 | 17,204.84 |
| 2006 | 1,296,375 | 5.54% | 3 | 17,954.80 |
| 2006 | 1,314,330 | 5.53% | 3 | 18,170.61 |

| ዓመት | የተላለፈ ሀብት ጠቅላላ መነሻ ዋጋ | የወለድ መክፈያ መጠን inflation rate | በዓመቱ የወራት ብዛት | የዋጋ ግሽበት መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 2006 | 1,332,501 | 5.55% | 3 | 18,488.45 |
| 2007 | 1,350,989 | 5.59% | 7 | 44,053.51 |
| ጠቅላላ የዋጋ ግሽበት | | | | 395,042.75 |

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የቋሚ ንብረቱ ዋጋና የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ | 1,395,042.75 |
| አጠቃላይ ከቋሚ ንብረቱ ሽያጭ የተገኘ ትርፍ | 4,957.25 |
| የሚከፈል ታክስ (15%) | 743.59 |

በአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አንድን የንግድ ሥራ ሀብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም የንግድ ትርፍ ግብር እና የካፒታል ዋጋ ዕድገት ታክስ እንደሚከፈልበት ያስቀምጣል፡፡ በዚሁ መሠረት ከንግድ ሥራ ሀብቱ የመዝገብ ዋጋ በላይ የሚገኘው ጥቅም በግብር ዓመቱ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተደምሮ የንግድ ትርፍ ግብር የሚከፈልበት ሲሆን ከንግድ ሥራ ሀብቱ ጠቅላላ ወጪ በልጦ የሚገኘው የገንዘብ መጠን ደግሞ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ግብር ይከፈልበታል ማለት ነው፡፡

<u>ለምሣሌ</u> ከላይ ABC ኃ.የተ.የግ.ኩባንያ ሕንጻውን በማስተላለፍ ያገኘው ጠቅላላ ገቢ 2,000,000 ብር ነው፡፡ የተላለፈው ሕንጻ ጠቅላላ ወጪ 1,109,435.1 ብር ሲሆን ሕንጻው በሚተላለፍበት ጊዜ የነበረው ቀሪ የመዝገብ ዋጋ ደግሞ 294,790.72 ብር ነው፡፡

ሥለሆነም ድርጅቱ በ850,000(1,400,000-550,000) በአመቱ ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ተደምሮ 30% የንግድ ትርፍ ግብር የሚከፈልበት ሲሆን በሌላ መልኩ 62,391.67(1,400,000-1,337,608.33) ደግሞ 15% የካፒታል ዋጋ ዕድገት ግብር ይከፈልበታል ማለት ነው፡፡

<u>በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት ምላሽ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተመለከተ</u>

በታክስ ኦዲት የሥራ ሂደት በኩል ውሳኔ እንዲሰጣቸው በመመሪያው የተለዩ የአገልግሎት ጥያቄዎች ሲቀርቡ እንደ ቅ/ጽ/ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ የአገልግሎት ጥያቄዎችን በስጋት ከተመረጡ ግብር ከፋዮች ጋር ተጣጥሞ የሚሰራበት ሁኔታ ማመቻቸት ከቅ/ጽ/ቤቶች የታ/ጉ/ም ሥራ አስኪያጆች እና የታክስ ኦዲት የሥራ ሂደት ኃላፊዎች የሚጠበቅ ሲሆን የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎችም በተቻለ መጠን በሙሉ የሥራ ጊዜ በሁሉም ቡድኖች ተካተው የሚሰሩበት አቅጣጫ ማስቀመጥ ተገቢ ሲሆን ውዝፍ የአገልግሎት ጣያቄዎች በሚኖሩባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በቅድሚያ

የአገልግሎት ጥያቄዎቹን ዓይነት መለየትና የአገልግሎት ጥቁዎችን ለማስተናገድ በወጣው መመሪያ መሠረት ውዝፍ ስራውን በጋራ ማጠናቀቅ ያስፈልጋል፡፡

የታክስ ኦዲት አሰራሩም መደበኛውን የሀገር ውስጥ ታክስ ኦዲት ማንዋልን የተከተለ እና የታክስና ሌሎች ህጎችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የዴስክ ኦዲት አሰራር ሂደትደረጃዎችና የሪፖርት ቅጾች

የአወሳሰን እና የተመላሽ አሰራር ሥርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን ከቅድመ ማጥራት እስከ ውሳኔ መስጠት ድረስ የሚከተሉትን ሦስት መደበኛ የኦዲት አሰራር ሂደት ደረጃዎች ተከትለው መከናወን አለባቸው፡፡

1. የዴስክ ኦዲት ቅድመ ኦዲት ትንተና/Pre-audit activities

አንድ የዴስክ ኦዲት ስራ ለታክስ ኦፊሰር ሲመራ በቅድሚያ የግብር ከፋዩን የንግድ ስራና ባህሪ፣ የዴስክ ኦዲት ሥራው ወሰኑና የሚሸፍነው ጊዜ እንዲሁም ምን ያህል የሰው ኃይልና የዴስክ ኦዲት ስትራቴጂ መከተል እንዳለብን ለመወሰን የቅድመ ትንተና ስራ መስራት ተገቢ ነው፡፡ ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1.1 የግብር ከፋይ የስራ ባህሪና የአገልግሎት አይነቶች እንዲሁም የግብር አከፋፈል ታሪክን ማጥናት/ Basic tax information

ይህም ማለት፡-

- → የታክስ ተመላሽ ጥያቄዎች እና ማሳወቂያዎች በጊዜውና በትክክል መቅረባቸውን፣
- → በየገቢ ሠንጠረዥ የሚጠበቁ የግብር/ታክስ ግዴታዎች ስለመሟላታቸው፣
- → ድርጅቶች የተሰማሩባቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች/የሚሰጧቸው አገልግሎቶችን ማወቅ፣
- → የታክስ ግዴታው በሕግ በተቀመጠው ጊዜ ስለመወጣቱ/Tax was paid on time/ እና
- → የሂሳብ መዝገቦች በታክስ አስተዳደርና በሌሎች ገዥ ሕጎች መሠረት የቀረቡ መሆኑን ወ.ዘ.ተ ማረጋገጥና ከዚህ ጋር በተገናኘ የተገኙ ጠቃሚ መረጃዎች ቅጂ ከዴስክ ኦዲት መረጃዎች ጋር ማያያዝ ይጠበቃል፡፡

1.2 ግብር የሚከፈልበት ገቢ እና ተከፋይ ታክስ በትክክል መሰላቱን ማረጋገጥ/ Review of the tax amount and taxable income

- → የኪሳራ ማቀናነስ ሕግን የተከተለ ስለመሆኑ ማረጋገጥ፣

→ ተቀናሽ መደረግ የማይገባቸውን ወጪዎች ከግ/ከፋዩ ገቢ ተቀናሽ አለመደረጋቸውን ማረጋገጥ፣

→ የገቢ ግብር ነፃ መብት ተጠቃሚነት መኖሩን ማየትና የተፈጻሚነቱን የግብር ዘመን እንዲሁም ግብር ወደ ሚከፈልበት ዘመን የተሻገሩ መሆኑን መመልከት፣

→ መከፈል የሚገባው የታክስ መጠን በሕጉ መሠረት መሰላቱን ምልከታ ማድረግ፣

→ የታክስ ማካካሻዎች/የተመላሽ ታክሶች/tax credit/ በትክክል የተሰሉ መሆኑን ወ.ዘ.ተ ይጠበቃል፡፡

## 1.3 <u>የሂሳብ መግለጫዎችን መገምገም/Financial statements review</u>

ከተለመደው የግብር አከፋፈል ልማድ(trend) ወጣ ያለ ነገር መኖሩን ለማረጋገጥ በዋና ዋና የሂሳብ ቋቶች እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑ የስሌት ማመዛዘኛዎችን(Essential ratios) በመጠቀም አመላካች ነጥቦችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የትርፋማነት ማመዛዘኛ(Profitability ratio) የግብር ከፋዩን ትርፋማነትና አቅም የሚያመላክት በመሆኑ ገቢውን ለማግኘት ከወጣው ወጪ እና ከድርጅቱ ሀብት ጋር በማነጻጸር ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ የተገኙ ጠቃሚ መረጃዎች ቅጂ ከዴስክ ኦዲት መረጃዎች ጋር ማያያዝ ይጠበቃል፡፡

## 1.4 <u>የካፒታል እና የአክሲዮን ባለቤትነት ለውጦች/Capital and shareholding changes</u>

ከካፒታል ወይም ከአክሲዮን ባለቤትነት ጋር በተያያዘ የተደረገ ማንኛውም ለውጥ ካለ ተረጋግጦ እና ተመዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

## 1.5 <u>የሶስተኛ ወገን መረጃዎችን መጠቀም /counterpart examinations</u>

የግብር ከፋዩን ገቢ ለማረጋገጥ ተቋሙ ከሚጠቀምበት የታክስ መረጃ ፖርታል በተጨማሪ ከሌሌሎች ተቋማት የሚከተሉትን በተመለከተ ዳሰሳ ማድረግ ይገባል፡፡

→ ከፋይናንስ ተቋማት የወሰድ ሞረጃን በተመለከተ፣

→ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች መረጃዎችን ማግኘት ለምሳሌ የትርፍ ድርሻን በተመለከተ፣

→ ከማህበራዊ ዋስትና ጽ/ቤቶች ጡረታና ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎችን በተመለከተ፣

→ በዋናነት ከድርጅቱ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተገናኘ አብዛኛውን ጊዜ ውል ከያዙባቸው ተቋሞች ጋር ውሉን/ክፍያን ወይም ሌሎች መረጃዎችን ጠይቆ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከኮንትራክተሮች ጋር በተያያዘ [illegible] መንገዶች



Ethiopian Revenue … Customs Authority

ባለስልጣን፣ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን፣ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላትና ግብዓት አቅራቢዎች ጋር ወ.ዘ.ተ ማረጋገጥ ይቻላል።

2. የዴስክ ኦዲት ዕቅድ ማዘጋጀት/ Planning the audit

አንድ የዴስክ ኦዲት ስራ በተጻፈ ዕቅድ መመራት ያለበት ሆኖ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

→ ቅድሚያ የተሰጣቸው ስጋቶች ዝርዝር፣

→ በስጋት ትንተና ወቅት በዋናነት ትኩረት ሊሰጣቸው የተለዩ ጉዳዮች፣

→ ስጋት አመላካች ጉዳዮችን ለማረጋገጥ የሚያስፈልግ መረጃ፤

→ ሥራዎችን በማከናወን ሂደት ልንከተላቸው የሚገቡ ቅደም ተከተሎች፣

→ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው ጊዜ እንዳስፈላጊነቱ በኃለፊው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚችል፣

→ በመጨረሻም ሥራው እንዲከናወን ስለመፈቀዱ በኃላፊው መረጋገጥ ይኖርበታል።

3. የዴስክ ኦዲት የኦዲት ሥራ መጀመር/Conducting the Audit

አንድ የኦዲት ሥራ ውጤታማ እንዲሆን፦

(i) በተመረጡ የስጋት አመላካች ነጥቦች ላይ ማተኮር፣

(ii) ሙያዊ ብቃት በተላበሰ እና ቅደም ተከተሉን ጠብቆ መሰራት፣

(iii) ትክክለኛና ዝርዝር ማጣቀሻ ሊቀርብለት የሚችል እና

(iv) በተቀመጠለት ጊዜ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

3.1 የባለሙያዎች ስብጥር/ Technical Ability

እንደ የግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ውስብስብነትና የዴስክ ኦዲቱ ከሚያተኩርባቸው ነጥቦች አንጻር ሥራውን የሚከናውኑ ባለሙዎች ልምድና ክህሎት ማቀናጀት የሚስፈልግ ሲሆን ይህም ከአመራሮች የሚጠበቅ ይሆናል።

3.2 የዴስክ ኦዲት ወሰንን ማስቀመጥ/Scope of Audit

ወደ ዴስክ ኦዲት ሥራ ከመገባቱ በፊት ሥራው የሚሸፍናቸው አንድና ከዚያ በላይ የሆኑ የዴስክ ኦዲቱ ጉዳዮች ወሰናቸው በአግባቡ መቀመጥ ያለበት ሲሆን ይህም ኦዲቱ ትኩረት በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲያተኩር እና አላሚውን እንዳይስት ያደርገዋል። የኦዲት

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

### 3.3 የዴስክ ኦዲት ስራ ወረቀቶችን ማደራጀት እና የኦዲት ስራ ማጠቃለል/Completing Working papers

ሁሉም የዴስክ ኦዲት የስራ ወረቀቶች የተከናወኑ ምርመራዎችና በየደረጃው የተደረጉ ውይይቶች የሚያሳዩ መሆን ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ተከታታይ ቁጥር እንዲይዙ በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያጣቅሱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

→ የግብር ከፋዮች መዛግብት/the taxpayer's records፣

→ በመረጃነት የተጠቀምንባቸው ሰነዶች ምንጭ/Source information documents

→ የውሳኔ ማስታወቂያ ማዘጋጀትና የቅርብ ኃላፊዎች ማረጋገጫ እንዲያገኝ ማድረግ፣

→ በቅርብ ኃላፊ በተሠጠ አስተያየት መሠረት ማስተካከያ ማድረግ፣

→ በዴስክ ኦዲት የተደረሰባቸው ግኝቶች ወደፊት ለሚደረግ የአመራር ግምገማና ዕቅድ በግብዓትነት እንዲያገለግል መዝግቦ መያዝ ፣

→ ሌሎች ማናቸውም ለዴስክ ኦዲት ሥራው ጥቅም ላይ የዋሉ መረጃዎች በባለሙዎችና የቅርብ ኃላፊዎች በአጭሩ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ግልፀኝነት እና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ለማስፈን የግብር ውሳኔ የተሰጣቸው የኦዲት ስራ ወረቀቶችና ከግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ እና ከሶስተኛ ወገን የተገኙ ማስረጃዎች ተደራጅተው ከኦዲት ዕቅድ ዝግጅት እስከ ውሳኔ ማስታወቂያ ያለውን ሂደት የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ መረጃዎች ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት በቦታው በማይኖሩበት ጊዜ ሌሎች ባለሙያዎች ያለምንም ችግር ከአቤቱታ እና ግብር ይግባኝ ለሚነሱ ክርክሮች በቂ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ተደርጎ የመስሪያ ወረቀቶች ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ ጋይድላይን በማንኛውም የሕግ አካላት በግ/ከፋዮች በማጣቀሻነት አያገለግልም፡፡

በ………………ቅ/ጽ/ቤት በመመሪያ ቁጥር 128/2009 መሠረት

በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል በዴስክ ኦዲት ተረጋግጦ ወደ ደንበኞች አገልግሎት የተላኩ የግብር ከፋይ አገልግሎት ጥያቄዎች ዝርዝር መግለጫ

የ----------- ወር ---------- ዓ.ም

| ተ.ቁ | የግብር ከፋይ ስም | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | የተጠየቀው የአገልግሎት ዓይነት | ጥያቄው ወደ ግብር አወሳሰን የቀረበበት ቀን | ለደንበኞች አገልግሎት ምላሽ የተላለፈበት ቀን | የተሰጠ ውሳኔ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

ያዘጋጀው
ስም ____________
ፊርማ ____________

ያረጋገጠው/የሥራ ሂደት
ስም ____________
ፊርማ ____________

ያፀደቀው/የታ/ጉዳይ ም/ሥራ አስኪያጅ
ስም ____________
ፊርማ ____________

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅፅ በቅርንጫፉ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት ተዘጋጅቶ ለዋናው መ/ቤት የየግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠ/ፕ/ል ዳይሬክቶሬት በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል።

በ………………ቅ/ጽ/ቤት በመመሪያ ቁጥር 128/2009 መሠረት

በደንበኞች አገልግሎት የተስተናገዱ የአገልግሎት ጥያቄዎች ዝርዝር መግለጫ

የ----------- ወር ---------- ዓ.ም

| ተ.ቁ | የግብር ከፋይ ስም | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | የተጠየቀው የአገልግሎት ዓይነት | ጥያቄው የቀረበበት ቀን | ለግብር ከፋዩ ምላሽ የተሰጠበት ቀን | የተሰጠ ውሳኔ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

ያዘጋጀው

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ያረጋገጠው/የሥራ ሂደት

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ያፀደቀው/የሞ/ኮ/ጉ/ም/ሥራ አስኪያጅ

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅፅ በቅርንጫፉ የደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ተዘጋጅቶ ለዋናው መ/ቤት የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል፡፡

በ.................ቅ/ጽ/ቤት በመመሪያ ቁጥር 128/2009 መሠረት

## የታክስ ኦዲት ስራ ተከናውኖ ወደ ደንበኞች የአገልግሎት የተላለፉ የአገልግሎት ጥያቄዎች ዝርዝር መግለጫ

የ------------ ወር ----------- ዓ.ም

| ተ.ቁ | የግብር ከፋይ ስም | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | የተጠየቀው የአገልግሎት ዓይነት | ጥያቄው ለታክስ ኦዲት የቀረበበት ቀን | ለደንበኞች አገልግሎት ምላሽ የተላለፈበት ቀን | የተሰጠ ውሳኔ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

**ያዘጋጀው**

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

**ያረጋገጠው/የሥራ ሂደት**

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

**ያፀደቀው/የታ/ት/ም/ሥራ አስኪያጅ**

ስም ____________________

ፊርማ ____________________

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅፅ በቅርንጫፉ የታክስ ኦዲት የስራ ሂደት የሥራ ሂደት ተዘጋጅቶ ለዋናው መ/ቤት የታክስ ኦዲት አሠ/ፐ/ል/ድ ዳይሬክቶሬት በየወሩ ሪፖርት የሚደረግ ይሆናል፡፡